# ትምህርት አምስት (የኦሪት ዘጸአት ጥናት)

►ዘጸአት ማለት ምን ማለት ነው?

ዘጸአት ሁለተኛው የሙሴ መጽሐፍ ሲሆን "ጸአት" ማለት መውጣት ማለት ነው፡፡ መውጣት ሲባል አንድን ቦታ ለቆ መውጣት ወይም ከባርነት ነፃ መውጣት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለእግዚአብሔር የተለዩት እስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት ነፃ እንደ ወጡና ወደ ከነዓን ምድር እንደተጓዙ እናነባለን፡፡ በአጠቃላይ እስራኤላውያን ከግብጽ የባርነት ኑሮ ነፃ መውጣታቸውንና ወደ ተስፋዪቱ ምድር ጉዞ መጀመራቸውን የሚተርክ መጽሐፍ ስለሆነ "ዘጸአት" ተባለ፡፡

►ዋናው የኦሪት ዘጸአት ታሪክ የሚጀምረው ከሙሴ ጋር መሆኑን ይታወቃል፡፡ ለመሆኑ ሙሴ ማን ነበር? የት ተወልዶ አደገ? ዋና ሥራውስ ምን ነበር?

ሙሴ እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብጽ ባርነት አውጥቶ እስከ ዮርዳኖስ ድረስ ለማድረስ የተጠቀመበት የእስራኤል መሪ ነበር፡፡ ሙሴ ከሌዊ ነገድ ግብጽ ውስጥ በተወለደ ጊዜ እስራኤላውያን በግብጽ ባርነት ነበሩ፡፡ የፈርዖን ሴት ልጅ "ከውሃ አውጥችሃለሁና" ስትል ሕፃኑን ሙሴ ብላ ሰየመችው (ዘጸ 2፡ 10)፡፡ ሙሴ አስቀድሞ በእናቱ እጅ በኋላም እንደፈርዖን የልጅ ልጅ ተቆጥሮ ሲያድግ እግዚአብሔርን እየፈራ የግብጽንም ትምህርት እየተማረ "በቃልም በሥራውም የበረታ ሆነ" (ዘጸ 2)፡፡

አርባ ዓመትም ሲሞላው በግብጽ ውስጥ በባርነት የነበሩትን እስራኤላውያን ወንድሞቹን ለመርዳት አስቦ ወደ እነርሱ ወጣ፡፡ ነገርግን አንዱን ግብጻዊ በቁጣ ተነሣሥቶ ከገደለ በኋላ ወደ ምድያም ሸሸ፡፡ ሴቶች ልጆቹንም ስለረዳቸው የምድያምን ካህን በቤቱ ተቀበለው፤ ከልጆቹም አንዲትዋን ዳረለት፡፡ ሙሴም እስከ አርባ ዓመት ድረስ የአማቱን በጎች በምድረ በዳሲ ጠብቅ ቆየ (ዘጸ 2፡ 11-25፤ዕብ 11፡ 24-26፤ሐዋ 7፡ 23-29)፡፡ እንደ አንዳንድ ሊቃውንት አገላለጽ ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን አገባ ይላሉ፤ አንዳንዶች ይህች የዮቴር ልጅ ሲፓራ ናት፤ ሌሎች ከግብጽ አገር ከእስራኤል ጋር የመጣች ሌላ ሴት ናት ይላሉ፡፡

►የሙሴና የእግዚአብሔር ወዳጅነት እንዴት ተጀመረ? ከእግዚአብሔር የተሰጠውስ ተልእኮ ምን ነበር?

ሙሴ በጎች በኮሬብ አቅራቢያ ሲጠብቅ ሳለ እግዚአብሔር ተገለጠለት፤ እስራኤልን ከባርነት እንዲያወጣ ወደ ፈርዖን ላከው፤ ወንድሙ አሮን እንዲናገርለት ፈቀደ(ዘጸ 3-4)፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከእግዚአብሔር ጋር ወዳጅነታቸው ተመሠረተ፡፡ የተሰጠው ተግባር እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ነፃ ማውጣት ነበር፡፡ ፈርዖንም ሕዝቡን አልለቅም ባለ ጊዜ እግዚአብሔር በሙሴ እጅ ዐሥር መቅሠፍት በግብጽ ላይ አወረደ(ዘጸ 5-10)፡፡ የግብጽ በኩር ልጆች ሁሉ በሞቱ ጊዜ የፋሲካን ደም በመርጨት ሙሴ ሕዝቡን በደህና ከግብጽ አወጣቸው(ዘጸ 12-13)፡፡ ፈርዖንም ተከተላቸው፤ እግዚአብሔርም የሙሴን ጸሎት ሰምቶ የኤርትራን ባሕር በመክፈል ሕዝቡን አዳነ(ዘጸ 14፡ 1-15፤ዕብ 11፡ 27)፡፡ በማራ፣ በኤሊምበራፊዲምም በኩል ወደ ሲና ሲጓዝ ሙሴ የሕዝቡን ማንጕራጕር እየታገሠ በጸሎት የሚያስፈልገውን ሁሉ ሰጣቸው፤ እጆቹንም ዘርግቶ በሚጸልይበት ጊዜ ጠላቶቻቸው በውሃ ሰጥመው ተሸነፉ(ዘጸ 15፡ 22-18፡ 27)፡፡

►እግዚአብሔር እንዴትና የት ቦታ ላይ ነው ለሙሴ ሕግን የሰጠውና ሙሴም ሕዝቡን ቃልኪዳን ያስገባው?

እስራኤላውያን ለአንድ ዓመት ያህል በሲና ሰፍረው ሳሉ በሙሴአ ማካኝነት ሕግን ተቀብለው ቅዱስ ሕዝብ እንዲሆኑለት ከእግዚአብሔር ጋር ቃልኪዳን ገቡ(ዘጸ 19-24)፡፡ሙሴ 40 ቀን በሲና ላይ በመቆየቱ ሕዝቡ ዐምፀው ለወርቅ ጥጃ ሰገዱ፡፡ ሙሴም ተቆጥቶ ጽላቱን መሬት ላይ ጣለው፤ ጣዖቱን ሰባበረ፤ ለሕዝቡ ግን ጸለየ፡፡ እንደገና 40 ቀን በተራራው ላይ ቆየ፤ እግዚአብሔርም ይቅር በማለት ቃልኪዳኑን እንደገና አጸናለት(ዘጸ 32-34)፡፡ ሙሴም የመገናኛውን የድንኳን መቅደስ አሠርቶ ተከለ(ዘጸ 35-40)፡፡ ስለ መሥዋዕትና ስለ ክህነትም ስለሚያደርጉትም ጉባኤ ሁሉ ትእዛዛትን ተቀበለ፤ ሕዝቡን ቈጠረ፤ በየነገዳቸውም በመቅደሱ ዙርያ እንዲሰፍሩ አደረገ፤ ለጉዞም አዘጋጃቸው(ዘኁ 1፡ 1-10)፡፡ እስከ ከነዓን ዳርቻም አደረሳቸው፤ ከአለማመን የተነሣ አንወጣም ካሉ በኋላ እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ እስከ 40 ዓመት ድረስ በምድረ በዳ ጠበቃቸው(ዘኁ 13፡ 1-19)፡፡

►ሙሴ በተቆጣ ጊዜ ግብጻዊውን እንደገደለና(ዘጸ 2) የተቀበለውንም ጽላት መሬት ላይ በመጣል እንደሰባበረው ተገልጿል(ዘጸ 32፡ 19)፤ ይህም ቁጣው እጅግ በጣም ነዶ እንደነበር ያሳያል፤ ሙሴ በባሕርዩ ምን ዓይነት ሰው ነበር?

ሙሴ በባሕርዩ እጅግ በጣም ትሑት ሰው ነበር፤ ግብጻዊውን በንዴት የገደለው ወገኖቹ የሆኑት እስራኤላውያን እጅግ በጣም የከፋ የባርነት ኑሮ ይኖሩ ስለ ነበርና እርሱም በወገኖቹ የስቃይ ኑሮ ተበሳጭቶ ስለ ነበር ነው፡፡ ሙሴ የእስራኤላውያን መቃወምና ማጉረምረም ብዙ ጊዜ የታገሠ ሰው ነው፡፡ ራሱንም ለእነርሱ አሳልፎ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን በጸሎቱ በመግለጽ እግዚአብሔር እንዳያጠፋቸው ለመነ(ዘጸ 32፡ 11-14፤ዘኁ 11፡ 1-15)፡፡ እስራኤላውያን በምድረ በዳ በሚንከራተቱባቸው ዓመታት መጨረሻ ላይ ግን አንድ ጊዜ ሙሴ ተቈጥቶ እግዚአብሔርን አላከበረምና ወደ ከነዓን እንዳይገባ ተከለከለ (ዘኁ 20፡ 1-13፤መዝ 106፡ 32-33)፡፡

►ሙሴ በእግዚአብሔር የተመረጠና የተጠራ ትሑትና ታማኝ አገልጋይ ከነበር የአገልግሎቱ ዋና ዋና ተግባራት የትኞቹ ነበሩ?

- ሙሴ የህዝቡ መሪና ፈራጅ ነበር(ዘጸ 18፡ 13-26)፡፡ እግዚአብሔር በሲና ሕግን ሰጥቶ ከእስራኤል ጋር ሳደረገው ቃልኪዳን ሙሴ መካከለኛ ነበር(ዘጸ 19፡ 7፤ገላ 3፡ 19)፡፡ እግዚአብሔር የሚመለክበትን ድንኳን መቅደስ አሠራ(ዘጸ 25-31 እናከ35-40)፡፡ በእጁም አሮንና ልጆቹን ለክህነት የለየ ለሕዝቡም የጸለየ ካህን ነበር(መዝ 99፡ 6፤ዘሌ 8 እና 9 ዘጸ 32፡ 30-32)፡፡ እግዚአብሔር "አፍ ለአፍ በግልጥ" ያናገረው እግዚአብሔርንም "ፊት ለፊት" ያወቀ ነቢይ ነበር(ዘኁ 12፡ 6-8፤ዘዳ 34፡ 10-12)፡፡ አብዛኛዎቹ በእጅ ስለ ተጻፉ አምስቱ የኦሪት መጻሕፍት "የሙሴ" ተብለው ይጠራሉ(ሉቃ 24፡ 27)፡፡

►በምን መልኩ ነው ሙሴ የክርስቶስ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው?

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተደጋጋሚ ሙሴ የክርስቶስ ምሳሌ እንደሆነ ከተገለጸባቸው ምክንያቶች ውስጥ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፦

ነቢይ በመሆኑ(ዘዳ 18፡ 15-19፤ሐዋ 3፡ 22)፤ በታማኝነቱ(ዕብ 3፡ 1-6)፤ የማደርያውን ድንኳን በመትከሉና በማገልገሉ(ዕብ 8-9) እንዲሁም በደረሰበት ተቃውሞ(ሐዋ 7፡ 35-40) ተደጋግሞ ተጠቅሷል፡፡ በኮሬብ በተገለጠው ክብር ፊቱ የበራ የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ በደብረታ ቦር የክርስቶስን የክብር መገለጥ አየ፡፡ ሙሴ አስቀድሞ በትንቢትና በምሳሌ ስለክርስቶስና ስለሞቱ ጻፈ(ዮሐ 5፡ 46፤ 3፡ 15)፤ ስለ ትንቢቱም መፈጸም በታቦር ከክርስቶስ ጋር እንዲነጋገር ዕድል አገኘ(ሉቃ 9፡ 30-31 ዘጸ 34፡ 29-35፤ 2ቆሮ 3፡ 7-18)፡፡

►ሙሴ ታቦት የተባለውን ቅዱስ ነገር እንደሠራ ይታወቃል፤ ለመሆኑ የዚህ ታቦት አሠራሩ እንዴትና ከምን ነበር? ዋና አገልግሎቱስ ምን ነበር?

ሙሴ በእርግጥ ከግራር እንጨት ታቦትን እንዲሠራ ታዘዘ። አሠራሩም ሣጥን ዓይነት ነበረ። ታቦቱ በወርቅ የተለበጠ መክደኛውም ከወርቅ የተሠራ ነበር፤ በላዩም ሁለት ኪሩቤል ተቀርጸዋል። የታቦቱ አገልግሎት የነበረው፦

1. ዐሠርቱ ቃላት የተጻፉባቸው የሁለቱ ጽላት ማኖርያ፤

2. ከእስራኤል መሪዎች ጋር የእግዚአብሔር መገናኛ ነበር። ስለዚህ ታቦቱ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የመኖሩ ምልክት ነበር (ዘጸ 25፡ 1-22፤ 40፡ 20)።

ሙሴ ታቦቱን አሠርቶ ሲያበቃ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ አኖረው። የእስራኤልም ሕዝብ ይዘውት ይጓዙ ነበር። በተለይም ዮርዳኖስን ሲሻገሩና ኢያሪኮን ሲዞሩ ካህናት ተሸክመውት ፊት ፊት ይሄዱ ነበር(ኢያ 3፡ 16)፤ የእስራኤል ሕዝብ ከኃጢአታቸው ሳይመለሱ በጦርነት እንደመከላከያ መሣርያ ሲሸከሙት ታቦቱ በመሳፍንት ዘመን በፍልስጤማውያን ተማረከ። ታቦቱ በእግዚአብሔር ስም የተጠራ ስለነበር እግዚአብሔር በፍልስጤማውያን ላይ ብዙ ተአምር አደረገ፤ ፍልስጤማውያንም መለሱት(1 ሳሙ 4-6) ። በኋላም ዳዊት ወደ ኢየሩሳሌም አመጣው። ሲያመጣውም ያዛ የተባለው ሰው በድፍረት ስለ ነካው ተቀሠፈ(2ሳሙ 6)፤ ሰሎሞንም ራሱ በሠራው ቤተመቅደስ አኖረው(1ነገ 8)። ታቦቱ በኢዮስያስ ዘመን በቤተመቅደስ ነበረ(2 ዜናመ. 35፡ 3)። በዚያን ጊዜ ነቢዩ ኤርምያስ ወደፊት የእስራኤል ሕዝብ ስለታቦቱ ምንም እንደማያስብ ትንቢት ተናገረ(ኤር 3፡ 16)።

ነቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ሲያፈርስ ታቦቱ የጠፋ ይመስላል። ምክንያቱም ዘሩባቤል በሠራው ቤተመቅደስ ታቦት አልነበረምና። በአዲስ ኪዳን የቃልኪዳኑ ታቦት በእግዚአብሔር ሰማያዊ መቅደስ እንደታየ ተጠቅሷል (ራእ 11፡ 19)።

►ሙሴ ከሲና ተራራና ከኮሬብ ጋር በተያያዘ መልኩ ብዙ ጊዜ ይጠቀሳል፤ ሙሴና ሲና ተራራ ግኑኙነታቸው ምንድን ነው?

ሲና ብዙ ጊዜ ተራራ እንደሆነ ሲጠቀስ ይደመጣል፤ ነገር ግን ሲና ተራራ ሳይሆን ብዙ ተራሮች በውስጡ የያዘ ወይም ያካተተ ከግብጽ አገር በስተምሥራቅና ከእስራኤል በስተደቡብ የሚገኝ አገር ነው። በሲና ምድረ በዳ እስራኤላውያን በሙሴ መሪነት 40 ዓመት እንደ ተጓዙ ይታወቃል (ዘጸ 19፡ 1)። ሌላው ደብረሲና የሚባለው ሲና ውስጥ ከሚገኙት ተራሮች አንዱ ሲሆን ዐሠርቱ ቃላት የተሰጡበት ተራራ ነው(ዘጸ 19፡ 20)። ይህ ደብረ ሲና ኮሬብም ተብሎ ይጠራል(ዘጸ 3፡ 1፤ዘዳ 4፡ 9-10)። ሙሴም ዐሠርቱ ቃላት በዚህ ተራራ ላይ ሆኖ ስለ ተቀበለ ስሙ በተደጋጋሚ ከዚህ ተራራ ጋር በተያያዘ መልኩ ይጠራል።

►ሙሴ ከሕግ ጋር በተያያዘ መልኩ ለምን ይጠቀሳል?

በመሠረቱ ሙሴ ከእግዚአብሔር ዘንድ በደብረ ሲና የተቀበላቸው ዐሠርቱ ቃላት ሕግ ስለነበሩ ከዚያ ጋር በተያያዘ መልኩ ሲጠቀስ ይታያል (ዘዳ 4፡ 13)። ትእዛዛቱ በቃልኪዳን መልክ ተሰጡ(ዘጸ 20፡ 1-17)። ሕግ አምስቱ የሙሴ መጻሕፍትን(ማቴ 5፡ 17፤ሉቃ 16፡ 16) እና ብሉይኪዳን በሙሉ (ዮሐ 10፡ 34፤ 12፡ 34) ሊያመለክት ይችላል። ለዚህ ነው ሙሴ ከሕግ ጋር በተያያዘ መልኩ የሚጠቀሰው።

►ዐሠርቱ ትእዛዛት የሚባሉት የትኞቹ ናቸው? ለምንስ ተሰጡ?

ዐሠርቱ ትእዛዛት የሚባሉት እግዚአብሔር በሙሴ አማካኝነት በደብረሲና ለእስራኤል የሰጣቸው የኪዳን ትእዛዛት ናቸው (ዘጸ 19፡ 5 — 20፡ 17)። ትእዛዛቱ በሁለት ጽላት በእግዚአብሔር ጣት የተጻፉ ናቸው(ዘጸ 31፡ 18)። ጽላቱም በታቦቱ ውስጥ ተቀመጡ (1ነገ 8፡ 9)። ከዓርባ ዓመታት በኂላ ወደ አገራቸው ሊገቡ ሲደርሱ ሙሴ ትእዛዛቱን በድጋሚ አስታወሳቸው። ሆኖም የእስራኤል ሕዝብ ሁኔታ አዲስ ስለሆነ ሰንበትን የማክበር ምክንያት ተለወጠ፤ የባልንጀራንም እርሻ ደግሞ እንዳይመኙ ታዘዙ(ዘዳ 5፡ 6-21)። በዘጸ 20፡ 2 መሠረት ዐሠርቱ ትእዛዛት የተሰጡት ደኅንነትን ተቀብሎ በቃልኪዳን ውስጥ ለሚገኘው የእስራኤል ሕዝብ ነው። የተሰጡበትም ምክንያት ደኅንነት ባለው ሕይወት እግዚአብሔርን እንዴት መከተል እንዳለባቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለቃልኪዳኑ ሕዝብ ለማስረዳትነው።

►ሰንበትን አክብር፤ ቀድሰውም ሲል የትኛውን ቀን ያመለክታል?ለምንስ መከበር ያስፈልገዋል? አለማክበርስ ምን ሊያስከትል ይችላል?

ሰንበት በዕብራይስጥ "ማቆም" "መተው" ማለት ነው። እስራኤላውያን ሰባተኛውን ቀን ለእግዚአብሔር እንዲቀድሱት ከላይ በተዘረዘሩት ዐሠርቱ ትእዛዛት ተነግረዋል(ዘጸ 20፡ 8-11)። ከዚህም በላይ ሰንበት በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል የቃልኪዳን ምልክት ነው(ዘጸ 31፡ 17)። በዚህም ምክንያት ሰንበትን አለማክበር ከባድ ቅጣትን ያስከትል ነበር(ዘኁ 15፡ 32-36)።

ሰንበት የእግዚአብሔር ሥራ እንዲታወስ ያደርጋል። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ስድስት ቀን ሠርቶ እንዳረፈ ሁሉ ሰውም በዚህ ዓለም ሠርቶ ወደ ዘለዓለም ዕረፍት አገራቸው ሲደርሱ ዐሠርቱ ቃላት በድጋሚ ተነገራቸው። ከዚህም ላይ ሰንበት እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብጽ ባርነት እንዳወጣቸው ያመለክታል(ዘዳ 5፡ 12-16)። እስራኤል ቀኑን በሚገባ ባለ ማክበራቸው በነቢያት ተወቅሰዋል(ሕዝ 20፡ 12-16፤አሞ 8፡ 6)፤ እንዲያከብሩትም ተስፋ ተሰጥቷቸዋል(ኢሳ 56፡ 2-4፤ 58፡ 13-14)። ነህምያ ሰንበትን አስከብሯል(ነህ 10፡ 31፤ 13፡ 15-22)። ኢየሱስ ሰንበትን አክብሯል(ሉቃ 4፡ 16)፤ የፈሪሳውያንን የሰንበት አከባበር ግን ተቃውሟል። እነርሱ ቀኑ እንዲከበር ብቻ እሸት ከመቅጠፍ፣ ድውይ ከመፈወስ እስኪ ከለክሉ ድረስ ብዙ ሕግና ወግ ደንግገው ነበር። ክርስቶስ ግን ከሰው ወግና ሥርዓት ምህረት እንደሚበልጥ አስተማረ(ማቴ 12፡ 1-14)።

►በአዲስ ኪዳን ዘመንስ እነዚህ ትእዛዛት ተሽረዋልን?

በአዲስ ኪዳን ዘመንም እነዚህ ትእዛዛት አልተሻሩም፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔርንና የሕዝቡን ግኑኝነት በማናቸውም ዘመን በቋሚነት ያስረዳሉ። በእነዚህ ትእዛዛት ውስጥ የሚታየው የእግዚአብሔር መሠረታዊ ፈቃድ "ታላቂቱና ፊተኛይቱ...ሁለተኛይቱም" በተባሉት ትእዛዛት ተጠቃልሎ ይገኛል(ማቴ 22፡ 36-40፤ሮሜ 13፡ 8-10)። እነዚህም፦ ከሁሉም የሚበልጠውና የመጀመርያው ትዕዛዝ የተባለው "እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም አሳብህ ውደድ" ሲሆን ይህንን የሚመስለው ሁለተኛው ትእዛዝ "ሰውን ሁሉ እንደራስህ አድርገህ ውደድ" የሚለው ነው።

ስለዚህ ትእዛዛቱ በቃልም ሆነ በመንፈስ በአዲሰ ኪዳን ይገኛሉ። በብሉይ ኪዳን ዘመን እንደታየው ሁሉ በአዲስ ኪዳንም የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መጠበቅ አለብን (ዮሐ 15፡ 14)። አዲስ ኪዳን እነዚህን ትእዛዛት ሕይወታችንን ለመምራት የሚያገለግሉ ናቸው(ገላ 4፡ 4-5)።

ትምህርቱ አዘጋጅ፦ አባ ምሥራቅ ጥዩ

የትምህርቱ አስተባባሪ፦ ተስፋዬ ባደገ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከመለሱ በኋላ ወደ ሀገረስብከቱ የተልእኮ ትምህርት ዝግጅት ክፍል ይላኩት።

የተማሪው/ዋ ስም ---------------------------------- ኮድ-------- ቁምስና------------------- ውጤት---------

1. ሙሴ እስራኤላዊ ወይም ከዕብራውያን ወገን ሆኖ እያለ በግብጻውያን ንጉሥ በፈርዖን ቤት ሊገኝና ሊያድግ እንደቻለ ከዘጸ 2 እንረዳለን። ከሚከተሉት ውስጥ የትኛውን ነው ሙሴ በፈርዖን ቤት የመገኘቱና የማደጉ ምክንያቶች ውስጥ የማይካተተው? ሀ) "ከዕብራውያን አዲስ የሚወለደውን ወንድ ልጅ ሁሉ እያነሣችሁ ዓባይ ወንዝ ውስጥ ጣሉ፤ ሴቶች ልጆች ግን በሕይወት ይኑሩ" የሚለው የንጉሡ ትእዛዝ ለ) ሕፃኑ መልከ መልካም መሆኑንና እናቱ እንዳይገደልባት በቅርጫት አድረጋ ወንዝ ዳር ማኖርዋን ሐ) የፈርዖን ሴት ልጅ ሕፃን ማሳደግ ትፈልግ ስለ ነበር ከዕብራውያን ሕፃናት አንዱ አምጡልኝ ብላ ማዘዝዋን መ) የሕፃኑ የሙሴ እኅት ወደ ፈርዖን ልጅ ወደ ልዕልቲቱ ሄዳ "ይህን ሕፃን እያጠባች የምታሳድግልሽ ከዕብራውያን ሴቶች አንዲት ሞግዚት ልጥራልሽን?" ብላ መጠየቋን ሠ) መልሱ የለም። አስተውል፦ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ አሪት ዘጸአት ምዕራፍ 1 እና 2 ቀድመው በደንብ ያንብቡ።

2. ሙሴ መንጋውን በኮሬብ ተራራ ሲጠብቅ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ በቁጥቋጦ ውስጥ በተቀጣጠለ የእሳት ነበልባል መካከል ሆኖ እንደ ተገለጠለት ይታወቃል፤ ከሚከተሉት ውስጥ የትኛውን ነው በዚያን ጊዜ ከተከናወኑት ነገሮች ውስጥ የማይካተተው ወይም ሐሰት የሆነው? ሀ) "የቆምህባት ምድር የተቀደሰች ስለሆነች ጫማህን አውልቅ" ተብሎ መታዘዙን ለ) ሙሴ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ማየቱን ሐ) እግዚአብሔር ስሜ "ያለሁና የምኖር ነኝ" ስሜም ለዘላለም ይኸውነው፤ ወደፊት የሚነሣው ትውልድ ሁሉ የሚያውቀኝ በዚሁ ስም ነው ማለቱን መ) ሙሴ የእግዚአብሔርን ጥሪ "የመናገር ችሎታ የለኝም፤ እኔ አንደበቴ የሚኮላተፍና አጥርቼ ለመናገር የማልችል ነኝ" ማለቱን ሠ) እግዚአብሐየር ሙሴን "ሌዋዊ የሆነው ወንድምህ አሮን አለ፤ እርሱ ጥሩ ተናጋሪነውና ይረዳሃል ማለቱን። አስተውል፦ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ዘጸ 4-5 በትኩረት ደጋግሞ ማንበብ ያስፈልጋል።

3. ሰንበት በዕብራይስ ጥቋንቋ "ማቆም" "መተው" ማለት እንደሆነ ከላይ ተገልጿል። ከሚከተሉት ውስጥ የትኛውን ነው ሰንበትን በተመለከተ ትክክለኛ ያልሆነው? ሀ) ሰንበት በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል የቃልኪዳን ምልክት ነው ለ) እንደ ብሉይ ኪዳን አገላለጽ ሰንበትን አለማክበር ከባድ ቅጣትን ያስከትላል ሐ) ኢየሱስ ሰንበትን አክብሯል፤ የፈሪሳውያንን የሰንበት አከባበር ግን ተቃውሟል መ) ዛሬም ቢሆን ሰንበትን በሚገባ አለማክበር እንደ ኃጢአት ይቆጠራል፤ ሰንበትን ያላከበረ ንስሓ መግባት ይኖርበታል ሠ) ሁሉም ትክክል ናቸው

4. በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተደጋጋሚ ሙሴ የክርስቶስ ምሳሌ እንደሆነ ከተገለጸባቸው ምክንያቶች ውስጥ ጥቂቶቹን ግለጽ። (ምላሽዎን በወረቀቱ በስተ ጀርባ በኩል ይጻፉት)።

5. ዐሠርቱ ትእዛዛት የሚባሉት እግዚአብሔር በሙሴ አማካኝነት በደብረሲና ለእስራኤል የሰጣቸው የኪዳንት እዛዛት መሆናቸው ይታወቃል (ዘጸ 19፡ 5 — 20፡ 17)። እነዚህ ዐሠርቱ ትእዛዛት በሁለት ይከፋላሉ፤ የሚከፈሉትም የተወሰኑት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ሁኔታ ስለሚመለከቱና ቀሪዎቹ ደግሞ ሰውን ወይም ሰው ከሰው ጋር የሚኖርበት ሁኔታ (ማኅበራዊ ግኑኝነትን) የሚመለከቱ ናቸው። ከእነዚህ ዐሠርቱ ትእዛዛት የትኞቹ ናቸው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን (እግዚአብሔርን የሚመለከት) እና ሰው ከሰው ጋር ያለውን ግኑኝነት (ሰውን የሚመለከት)? ዐሠርቱ ትእዛዛት በሁለት መከፈላቸውን ከፋፍለው ያሳዩ።